# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
# በሰሜን አሜሪካ አኅጉረ ስብከት
# የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጉባኤ

## የክፍለ ግዛቶች መዋቅርና የሥራ መመሪያ
## በ15ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ለውይይት ቀርቦ የጸደቀ

**በዳላስ ቴክሳስ**

**ነሐሴ 30, 2007 ዓ.ም**

# ማውጫ


- ❖ መግቢያ ........................................................................ 3
- ❖ ስያሜ ........................................................................ 4
- ❖ ትርጓሜ ........................................................................ 4
- ❖ የክፍለ ግዛት አከላለል ................................................ 4
- ❖ የክፍለ ግዛት ጠቅላላ ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነት ........................ 5
- ❖ የክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት ...................... 5
- ❖ የክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ ክፍሎች ዝርዝር ........................ 5
- ❖ የክፍለ ግዛት የሥራ አስፈጻሚ አባላት የሥራ ድርሻ .................. 6
- ❖ ምርጫን የተመለከቱ ነጥቦች ........................................ 8
- ❖ ልዩ ልዩ ነጥቦች ................................................ 8

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
## በሰሜን አሜሪካ አኅጉረ ስብከት የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ

# የክፍለ ግዛት መዋቅር እና የሥራ መመሪያ

### መግቢያ

የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በሰሜን አሜሪካ ያሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በኅብረት ሆነው በቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚጠበቅባቸውን ተሳትፎ እንዲያበረክቱ አድርጓል እያደረገም ይገኛል። የአገልግሎት አድማሱ እየሰፋ ሲመጣም ለአሠራር ያመች ዘንድ የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው እሙን ነው።

ስለዚህ አንድነት ጉባኤ ባለው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አባላቱ የሚያበረክቱትን ተሳትፎ የበለጠ የተጠናከረ እና የጉባኤው ሥራ አመራር በቀላሉ ለመከታተል እንዲያስችለው ለማድረግ ይህ የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ በ8ኛው እና በ13ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ የጸደቀውን የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ መሠረት አድርጎ ተዘጋጅቷል። ተፈጻሚነቱም በ2003 ዓ.ም የወጣውን የአንድነት ጉባኤውን መተዳደሪያ ደንብ የተከተለ ነው።

የዚህ መዋቅር እና የሥራ መመሪያ መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት በ13ኛው መደበኛ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ ቀርቦ በጸደቀው የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ ላይ የሚከተሉትን ማሻሻያዎች ለመጨመር እና አገልግሎቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማስኬድ ነው።

1) በዞን መዋቅር ሥር የታቀፉት ሰንበት ት/ቤቶች በንግሥ በዓላት እና በጉባኤያት በአካል እንዲገናኙበት የሚያደርግ አከላለል በማስፈለጉ።
2) የአንድነት ጉባኤው ሥራ አመራር የአገልግሎት ዘርፎች ከክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ የአገልግሎት ዘርፎች ጋር የተሰናሰሉ እንዲሆኑ ለማድረግ።
3) የቀድሞውን የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ ወቅታዊ ለማድረግ እና ወደ ሥራ እንዳይተረጎም ያደረጉ ነጥቦችን ለማሻሻል።

በዚህ የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ የተሻሻሉ ዋና ዋና ነጥቦች፡-

1) የክፍለ ግዛት ቁጥር ከ 7 ወደ 9 ከፍ ተደርጓል።
2) የክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ ተግባር፤ ኃላፊነት እና ክፍሎች የተወሰነ ለውጥ በማድረግ ክፍሎችን ከ5 ወደ 9 ከፍ ተደርጓል።
3) የአንዳንድ ክፍሎች የሥራ ኃላፊነት ማስተካከያዎች ተደርገዋል።

በቀድሞው የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ ላይ እንደተጠቀሰው ሰሜን አሜሪካ ሰፊ ሀገር በመሆኑና አባላቱም በተለያየ ክፍለ ግዛት ተራርቀው በመገኘታቸው በአንድ አቅጣጫ ያሉት ሰንበት ት/ቤቶች በየጊዜው እየተገናኙ ስለ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ልምድ እንዲለዋወጡ ለማድረግ እና ለመሰል ዓላማዎች ለማከናወን ሲባል ይህ የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ ለሦስተኛ ጊዜ ተዘጋጅቷል።

ይህ የክፍለ ግዛቶች መዋቅር እና የሥራ መመሪያ ነሐሴ 30/2007 ዓ.ም በ15ኛው መደበኛ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ ቀርቦ የጸደቀ እና በጉባኤው ውሳኔ መሠረት አገልግሎት ላይ የዋለ።

## አንቀጽ አንድ

### ስያሜ

በኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን በሰሜን አሜሪካ አኅጉረ ስብከት የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጉባኤ የክፍለ ግዛት ጠቅላላ ጉባኤ እየተባለ ይጠራል።

## አንቀጽ ሁለት

### ትርጓሜ

ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ በዚህ የመዋቅር እና የሥራ መመሪያ፡-

2.1 <u>አንድነት ጉባኤ ማለት፡-</u> በኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን በሰሜን አሜሪካ አኅጉረ ስብከት የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጉባኤ ማለት ነው።

2.2 <u>ክፍለ ግዛት ማለት፡-</u> በሰሜን አሜሪካ በአንድ አቅጣጫ ባሉ ግዛቶች/ስቴቶች/ የሚገኙ በንግሥ በዓላት ወይም በጉባኤያት በቅርብ ሊገናኙ የሚችሉ ሰንበት ት/ቤቶችን ያቀፈ እና ተጠሪነቱ ለአንድነት ጉባኤው ሥራ አመራር የሆነ አካል ነው።

2.3 <u>የክፍለ ግዛት ጠቅላላ ጉባኤ ማለት፡-</u> በአንድ ክፍለ ግዛት ውስጥ ያሉ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በዓመት ሦስት ጊዜ ሁሉም አባላት ወይም የሰ/ት/ቤቶች ተወካዮች በተገኙበት ስለ ክፍለ ግዛቱ አገልግሎት አጠቃላይ እንቅስቃሴ ግምገማ የሚወያዩበት ጉባዔ ነው።

## አንቀጽ ሦስት

### የክፍለ ግዛት አከላለል

የክፍለ ግዛት አከላለል በሰሜን አሜሪካ በሁሉም አካባቢ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት በ10 ክፍለ ግዛት የከፈለ ነው። ወደፊት ግን የአንድነት ጉባኤው መዋቅር በተሞክሮ እየታየ ሲመጣና ሲጠናከር የአከላለሉ መሰረታዊ የሆኑ ነጥቦች ሊካተቱበትና እንደገና ሊታይ ይችላል።

የክፍለ ግዛት ዝርዝርና በውስጣቸው የተካተቱት የሰሜን አሜሪካ ግዛቶች/ስቴቶች/ እንደሚከተለው ቀርቧል።

| | የክፍለ ግዛቱ ስም | የሚያካልለው ክፍለ ግዛት |
|---|---|---|
| 1 | ሰሜን ምዕራብ / North West | ዋሽንግተን፤ ኦሪገን፤ አይዳሆ፤ ሞንታና |
| 2 | ምዕራብ / West | ካሊፎርኒያ፤ አሪዞና፤ ኔቫዳ፤ ዩታ |
| 3 | መካከለኛው / Mid | ሳውዝ ዳኮታ፤ ኖርዝ ዳኮታ፤ ሚኒሶታ፤ አይዋ |
| 4 | መካከለኛው ደቡብ / Mid South | ኔብራስካ፤ ካንሳስ፤ ኮሎራዶ፤ ዋዩሚንግ፤ ሚዞሪ |
| 5 | መካከለኛው ምዕራብ / MidWest | ዊስከንሰን፤ ኢሊኖይስ፤ ኢንዲያና፤ ኦሃዮ፤ ሚቺጋን |
| 6 | ደቡብ ምሥራቅ / South East | ሳውዝ ካሎራይና፤ ኖርዝ ካሎራይና፤ ጆርጂያ፤ አላባማ፤ ፍሎሪዳ፤ ቴኔሲ፤ ኬንታኪ፤ ሚሲሲፒ |
| 7 | ምሥራቅ / East | ዋሽንግተን ዲሲ፤ ቨርጂኒያ፤ ሜሪላንድ፤ ኒውጅርሲ፤ ዌስት ቨርጂኒያ፤ ዴላዌር፤ ፔኒሲሊቫኒያ |
| 8 | ደቡብ / South | ቴክሳስ፤ ኒው ሜክሲኮ፤ ኦካላሆማ፤ አርካንሳስ፤ ሉዚያና |
| 9 | ሰሜን ምሥራቅ / North East | ሜያን፤ ማሳቹሴትስ፤ ቬርሞንት፤ ኒውሃምፕሺር፤ ሮሆድ አይላንድ፤ ኒውዮርክ፤ ከነቲኬት |

## አንቀጽ አራት

### የክፍለ ግዛት ጠቅላላ ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነት

የክፍለ ግዛት ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

4.1 በክፍለ ግዛቱ የሥራ አስፈጻሚ ጉባዔ በሚቀርብለት መሠረት በግዛቱ ሊሠሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ያቅዳል።
4.2 የክፍለ ግዛቱን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል።
4.3 የክፍለ ግዛቱን የሥራ አስፈጻሚ ጉባዔ አባላት ይመርጣል።
4.4 በዓመት ሦስት ጊዜ ጠቅላላ ጉባዔ ያደርጋል።
4.5 በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ የሥራ አስፈጻሚ ይመርጣል።

## አንቀጽ አምስት

### የክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት

የክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ ከዚህ በታች የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

5.1 የክፍለ ግዛቱን አጠቃላይ የሥራ ሂደት ይከታተላል። በሥሩ አሉ አባላት መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በአግባቡ መወጣታቸው ይገመግማል።
5.2 በክፍለ ግዛቱ ሊሠሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ያቅዳል።
5.3 የክፍለ ግዛቶች ጉባኤ አዘጋጇል።
5.4 በክፍለ ግዛቶች ጉባኤ ላይ የሚገኙ አባቶችን መምህራንና ተጋባዦችን እንዲሁም የስብሰባውን አጀንዳዎች ይወስናል።
5.6 በሥራ አገልግሎት ሂደት የደከሙ የአገልግሎት ክፍሎችን በመወያየት ይተካል።
5.7 ክፍለ ግዛቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከሰንበት ት/ቤቶች ጋር በቅርበት በመገናኘትና በመመካከር ይሰራል።

## አንቀጽ ስድስት

### የክፍለ ግዛት ሥራ አስፈጻሚ ክፍሎች ዝርዝር

የክፍለ ግዛቶች የሚከተሉት ሥራ አስፈጻሚ አባላት ይኖሩታል የሚከተሉት

6.1 ሰብሳቢ
6.2 ጸሐፊ
6.3 ሒሳብ ክፍል
6.4 ትምህርትና ሥልጠና ክፍል
6.5 ግንኙነት ክፍል
6.6 በጎ አድራጎት ክፍል
6.7 መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል
6.8 የልማትና የሽያጭ ልማት ክፍል
6.9 የጥናትና ዕቅድ ክፍል

## የክፍለ ግዛት የሥራ አስፈጻሚ አባላት የሥራ ድርሻ

### 6.1 የሰብሳቢ የሥራ ኃላፊነት

6.1.1 በመደበኛም ሆነ በአስቸኳይ ጊዜ የተጠራውን ስብሰባ ይመራል።
6.1.2 የክፍለ ግዛቱን የሥራ እንቅስቃሴ በወጣለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከጸሐፊው ጋር በመሆን ለአንድነት ጉባኤው ሥራ አመራር እና በክፍለ ግዛት አባላት ሪፖርት ያደርጋል።
6.1.3 ለቅርንጫፉ የሥራ እንቅስቃሴ ገንዘብ ወጭ እየተደረገ ከሆነ ከሒሳብ ክፍል ጋር በመሆን ሥርዓት ባለው መልኩ ይተገብራል።
6.1.4 በዋናው የአንድነት ጉባኤ ሥራ አመራር የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ሥራን ያግዛል።

### 6.2 የጸሐፊ የሥራ ኃላፊነት

6.2.1 ተጠሪነቱ ለክፍለ ግዛቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል።
6.2.2 የክፍለ ግዛቱን የጽሕፈት ሥራዎች ያከናውናል።
6.2.3 ከሰብሳቢው ጋር በመሆን የክፍለ ግዛቱን ዕቅድ ከአገልግሎት ክፍሎች በማሰባሰብ ያቀናጃል፤ ሲፀድቅም አፈፃፀሙን ይከታተላል።
6.2.4 ሰብሳቢው በሌለበት ስብሰባ ይመራል።
6.2.5 አጠቃላይ የክፍለ ግዛቱን የስራ ክንውን ሪፖርት ለክፍለ ግዛቱ አባላት ያቀርባል፤ ለዋናው የአንድነት ጉባኤ ጽፈት ቤት ይልካል።

### 6.3 የሒሳብ ክፍል የሥራ ኃላፊነት

6.3.1 ተጠሪነቱ ለክፍለ ግዛቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል።
6.3.2 የክፍለ ግዛቱን የሒሳብ መዛግብት በተሟላ ሁኔታ አዘጋጅቶ ገቢና ወጪውን ይመዘግባል።
6.3.3 ከአባላት የተሰበሰበውን ገንዘብ ወደ አንድነት ጉባኤው የሂሳብ አካውንት ያስገባል፤ ተገቢውንም መረጃ ይይዛል።
6.3.4 ለክፍለ ግዛቱ ሥራ ማስኬጃ የሚሆን ከ200 - 500 የተመደበውን ተንቀሳቃሽ ገንዘብ በኃላፊነት ይይዛል።
6.3.5 የክፍለ ግዛቱን ዓመታዊ የሒሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል/ያቀርባል። ለክፍለ ግዛቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፤ ለዋናው የሂሳብ ክፍልም የተዘጋጀውን ዓመታዊ ሪፖርት በግልባጭ ያሳውቃል።
6.3.6 ከአባላት ሆነ ከማናቸውም በጎ አድራጊዎች በሕጋዊ መንገድ የሚገኘውን የገንዘብ አስተዋጾ እንደዚሁም፤ ከሽያጭ፣ ከጨረታ እና ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚገኙትን ገቢዎችን ይሰበስባል።
6.3.7 ከክፍለ ግዛቱ ሰብሳቢ ጋር በመሆን የግዛቱን ሒሳብ ያንቀሳቅሳል።
6.3.8 በአንድነት ጉባኤውን ስም በተመለከተ ለሚደረግ ማንኛውም ዓይነት የገንዘብ አስተዋጽኦ ሆነ በጎ አድራጎት ስራ ወይም ልገሳ፤ ገንዘቡ በመጀመሪያ ከበቂ መረጃዎች ጋር ወደ ዋናው የባንክ አካውንት መግባት ይጠበቅበታል። ከዚያም ለአስፈላጊው ድጎማ ወጪ የሚደረገው ከዋናው አካውንት ይሆናል። ክፍለ ግዛቱና የወጣበት ምክንያት በቼኩ ላይ ይጠቀሳል።
6.3.9 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

## 6.4 የትምህርትና ሥልጠና ክፍል የሥራ ኃላፊነቶች

6.4.1 ተጠሪነቱ ለክፍለ ግዛቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል።
6.4.2 ከአንድነት ጉባኤው የሚላኩ ትምህርቶችን፣ በራሪ ጽሁፎችን ለአባላት ያሰራጫል።
6.4.3 ከሰ/ት/ቤቶች ጋር በመተባበር የክፍለ ግዛቱ ጉባኤያት እንዲደረጉ ያደርጋል።
6.4.4 ከአንድነት ጉባኤው ትምህርት ክፍል ጋር በመቀናጀት የሥልጠና መርሐ ግብሮችን ያዘጋጃል።
6.4.5 የአብነት ትምህርት የሚስፋፉበትንና በሰ/ት/ቤቶች ደረጃ በተጠናከረ መንገድ የሚሠጥበትን መንገድ ይቀይሳል።
6.4.6 ከቤተክርስቲያን አባቶች ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ ትምህርቶችን በሲዲ፣ ዲቪዲ እና ቪሲዲ እንዲዘጋጁ በማድረግ ለአባላት ያሰራጫል።
6.4.7 ዌብ ሳይት ላይ የሚወጡ ሥራዎችን አሰባስቦ ለዋናው ትምህርት ክፍል ይልካል።
6.4.8 ዜናዎችን ይዘግባል።
6.4.9 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

## 6.5 የግንኙነት ክፍል የሥራ ኃላፊነት

6.5.1 በሰንበት ት/ቤቶች መካከል የእርስ በእርስ ትውውቅና የአገልግሎት ልምድ ልውውጥ እንዲኖር ያደርጋል።
6.5.2 ከአንድነት ጉባኤው አባላት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያደርጋል፤ ስለ እያንዳንዱ አባል ዝርዝር መረጃ ይይዛል፣ ለአንድነት ጉባኤው ግንኙነት ክፍልም ይልካል።
6.5.3 በክፍለ ግዛቱ በአባልነት የታቀፉ ሰ/ት/ቤቶች ስለ አንድነቱ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተገቢውን ሥራ ይሰራል።
6.5.4 ለአባላት የእንኳን አደረሳችሁና የበዓላት መልዕክቶችን ከዋናው ግንኙነት ክፍል ጋር በመቀናጀት ይልካል።
6.5.5 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

## 6.6 የበጎ አድራጎት ክፍል የሥራ ኃላፊነት

6.6.1 በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ገዳማትንና አድባራትን እንዲሁም የአብነት ትምህርት ቤቶችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመርዳት እንዲቻል ከዋናው የበጎ አድራጎት ክፍል ጋር በመተባበር እርዳታዎችን ያስተባብራል።
6.6.2 የአንድነት ጉባኤው አባላት ችግር ሊያጋጥማቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የሚረዱበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
6.6.3 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

## 6.7 መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል የሥራ ኃላፊነት

6.7.1 ኦርቶዶክሳዊ መዝሙሮችን ያሰባስባል፤ ከግንኙነት ክፍል ጋር በመተባበር ሰንበት ት/ቤቶች እንዲያገኙ ያደርጋል።
6.7.2 የሥነ ጽሑፍ ተሰጥዖ ያላቸው አካላትን በማስተባበር በተለያዩ ርዕሶች አስተማሪ የሆኑ ድርሰቶችን ያሰባስባል፤ ለሚመለከተው አካልም ይልካል።
6.7.3 ከቤተክርስቲያን የዜማ አባቶች ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ መዝሙሮችን በሲዲ፣ ዲቪዲ እና ቪሲዲ እንዲዘጋጁ በማድረግ ለአባላት ያሰራጫል።

6.7.4 ዌብ ሳይት ላይ የሚወጡ ሥራዎችን አሰባስቦ ለዋናው መዝሙር ክፍል ይልካል።
6.7.5 ከዋናው ሥራ አመራር የመዝሙር እና ሥነጥበባት ጋር በመተባበር ሥራዎችን ይሠራል።
6.7.6 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

## 6.8 የልማትና የሽያጭ ልማት ክፍል የሥራ ኃላፊነት

6.8.1 በአንድነት ጉባኤው የሚዘጋጁ መጽሔት/ጋዜጣ ካለ ለአባላት በጊዜው እንዲያደርስ ያደርጋል። የየሽያጭ ገንዘቦችንም በማሰባሰብ ለሒሳብ ክፍል ገቢ ያደርጋል።
6.8.2 የገንዘብ ምንጭ የሆኑ የልማት ሥራዎችን ያከናውናል።
6.8.3 የተሰበሰበውን ገንዘብ ለክፍለ ግዛቱ ሒሳብ ክፍል ገቢ ያደርጋል፤ ተገቢውንም መረጃ ይይዛል።
6.8.4 በክፍለ ግዛቱ ያሉትን የማኅበሩን ንብረቶች መዝግቦ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል።
6.8.5 የዋናው ሥራ አመራር ልማት ክፍል ሥራን ያግዛል።
6.8.6 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

## 6.9 የጥናትና ዕቅድ ክፍል የሥራ ኃላፊነት

6.9.1 ለአንድነት ጉባኤውና ለክፍለ ግዛቱ ማደግና መስፋፋት የሚጠቅሙ ጥናቶችን ያዘጋጃል ጥናቶች እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።
6.9.2 ከዋናው ሥራ አመራር የጥናት እና እቅድ ክፍልን ጋር ሥራ ይሰራል።
6.9.3 በክፍለ ግዛቱ አዳዲስ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል።
6.9.4 የክፍለ ግዛቱ የአገልግሎት ክፍሎች ዕቅድ በአንድነት በማዘጋጀት ለሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል።
6.5.5 የክፍሉን የሥራ ክንውን ለሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያቀርባል።

# አንቀጽ ሰባት

## ምርጫን የተመለከቱ ነጥቦች

7.1 የክፍለ ግዛቱ ሥራ አስፈጻሚ በየሁለት ዓመቱ ይመረጣል።
7.2 አንድ አባል በተከታታይ ከሁለት ላልበለጠ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል።
7.3 የክፍለ ግዛቱ የሥራ አስፈጻሚ ምርጫ በሚደረግበት ዓመት የዋናው የሰ/ት/ቤቶች አንድነት ጉባዔ ሥራ አመራር ምርጫ በሚደረግበት ዓመት አይሆንም። ይህም በክፍለ ግዛቶችና በዋናው ሥራ አስፈጻሚ መካከል የአሠራርና ግንኙነት ክፍተት እንዳይፈጠር ያግዛል።
7.4 ምርጫው የሚደረገው በጉባዔው ደንብ መሠረት በተቀመጡት ነጥቦችና ለምርጫ ተብሎ የተዘጋጀውን የምርጫ መስፈርት ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ አባላትን መጠቆምና በእጩዎች ላይ አባቶች ውዳሴ ማርያም አድርሰው እጣ እንዲወጣ ይደረጋል።
7.5 ከሥራ አስፈጻሚ አባላት መካከል አንድ አባል ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብና እንዲሁም ክፍሉን በትክክል እንዳልመራ ሥራ አስፈጻሚው ካመነበት በምትኩ ሌላ ተክቶ ሊያሠራ ይችላል።
7.6 ተመራጭ እጩዎች ሲመረጡ ከተቻለ ከተለያየ ግዛት (እስቴት) እና ሰንበት ት/ቤቶች ቢሆኑ ይመረጣል።

## አንቀጽ ስምንት

### ልዩ ልዩ ነጥቦች

8.1 እያንዳንዱ ክፍለ ግዛት ተጠሪነቱ ለዞን ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል።
8.2 ክፍለ ግዛቶች ከአንድነት ጉባዔው ውጪ ከሆነ አካል ጋር ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም።
8.3 የክፍለ ግዛቶች የሥራ አስፈጻሚ ስብሰባዎች በሥርዓተ ቤተክርስቲያን መሠረት በጸሎት ይጀመራሉ።
8.4 ስብሰባውም ከተሳታፊዎች መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ሊካሄድ ይችላል።
8.5 የየክፍለ ግዛቱ አስፈጻሚዎች ከተለያዩ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ስለሚሆኑ በሚቻለው ሁሉ በአካልና በስልክ እየተገናኙ ሥራዎችን ሊሠሩ ይችላሉ።

## አንቀጽ ዘጠኝ

ይህ መመሪያ ወደፊት እየታየ በአንድነት ጉባዔው ሥራ አመራር ሲታመንበት ሊሻሻል ይችላል።